**<u>ሱዳን ሀገራችን ላይ አለኝ የምትለው የመሬት ጥያቄ በእጅጉ የተጭበረበረና ፈጽሞ ተገቢ ያልሆነ ስለመሆኑ!!!</u>**

መሰንበቻውን የሱዳን ጦር ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሚካናይዝድ ደረጃ ዘምቶ የሀገራችንን ሉዓላዊነት በመዳፈር ድንበር ጥሶ እስከ 50 ኪ.ሜ. ድረስ ወደ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ሱዳን "ይገባኛል!" ከምትለውና "ለ25 ዓመት ያህል ከእጃችን ወጥቶ የነበረውን መሬት ከ70-80% የሚሆነውን አስመልሻለሁ ቀሪውንም ከሰሞኑ አስመልሳለሁ!" በማለት እየተናገረ ይገኛል!!!

"ለ25 ዓመት ያህል...!" ያሉት ወያኔ 1983ዓ.ም. ሥልጣን እንደያዘ ለሱዳን ቃል እንደገባው በትግሉ ወቅት ለዋለችለት ውለታ ወረታዋን ለመመለስ ገበሬውን አፈናቅሎ መሬቱን ለሱዳን ሰጥቶት ለአምስት ዓመት እንደቆዩ በግብጹ መሪ በሆስኒ ሙባረክ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ በሱዳን የተደገፈ የግድያ ሙከራ በመደረጉ ምክንያትና ሱዳን ተፈላጊዎቹን "አሳልፌ አልሰጥም!" በማለቷ ምክንያት የሱዳንና የወያኔ ግንኙነት ሻክሮ ሰጥቷቸው የነበረውን መሬት መልሶ ቀምቷቸው እስከ አሁን ስለቆዩ ነው እንጅ "ለ25 ዓመት ከእጃችን ወጥቶ የነበረውን!" ያሉት ወያኔ ሥልጣን ከመያዙ በፊት ግን መሬቱ በእጃቸው ስለነበረ እንዳይመስላቹህ!!!

እኔ ሱዳኖች አሁን ድንበር ጥሰው የገቡት በጉልበታቸው መሬቱን የእነሱ ለማድረግ በማሰብ ነው የሚል እምነት የለኝም። "የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል!" እንዲሉ አገዛዙ ግርግሩን ተጠቅሞ "በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በመሸፈጥ ወይም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ በማሴር ገብተው እንዲይዙት አድርጓል!" የሚል እምነት ነው ያለኝ። ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅን "ተወረርኩ!" ብሎ መወረሩን ያላስታወቀውና ክስ ያላሰማውም ለዚያ ነው። ለማስመሰል ያህል ግን ለእኛ መቃወሙን በለሆሳስ አሰምቷል!!!

አገዛዙ ሱዳኖች በሐሰተኛና በተጭበረበረ ጥያቄ "የእኛ ነው!" የሚሉትን መሬት በጥያቄያቸው መሠረት "የእነሱ ነው!" ብሎ አምኖ ከሆነ መሬቱን እንዲይዙት ያደረገው እየተገነባ ያለው የዓባይ ግድብም የሱዳን መሬት ውስጥ እንዳለ አድርጎ ማመኑንና መቀበሉን ሊያውቅ ይገባል!!!

እውነታው ግን ሱዳን "በዚህ ስምምነት መሠረት ድንበራችንን መካለል አለበት!" እያለች የምታቀርበው "ዐፄ ምኒልክ ከወቅቱ የሱዳን ቅኝ ገዥ ከእንግሊዙ ተወካይ ከሌፍተናንት ኮሎኔል ጆን ሊን ሀሪንግተን ጋር እ.ኤ.አ. በ1902ዓ.ም. ተስማምተውበታል!" የምትለው ከታች በምታዩት ካርታ መሠረት እንኳ እራሱ ብንካለል እኛ ከሱዳን ልንወስደው የሚገባን የአንዳንድ ሀገሮችን የቆዳ ስፋት የሚበልጥ መሬት አለን እንጅ ሱዳን ከእኛ ልትወስድ የምትችለው ስንዝር መሬት እንኳ አይኖራትም!!!

ይሄንን ለመረዳት የግድ የካርታ ባለሞያ መሆን አይጠይቅም። ፕሮጀክተር ካላቹህ ከታች ያለውን ካርታ አሁን በእጃቹህ ካለው ዘመናዊ የኢትዮጵያ ካርታ ጋር አደራርባቹህ ወይም overlap አድርጋቹህ ለመመልከት ሞክሩ ጭራሽ እኛ ከእነሱ መጠየቅ ያለብን በርካታ መሬት ያለን መሆኑን ትረዳላቹህ እንኳን የምንሰጣቸው ሊኖር ቀርቶ!!!

ያያያዝኩላቹህ ሁለቱ ካርታዎች አንደኛው "ዐፄ ምሊልክ ማኅተማቸውን አሳርፈውበታል!" የሚባለው ነው። የካርታውን ገጽ ሁለት ማለትም ወደላይ የዓባይ ግድብ እየተገነባ ካለበት እስከ ኤርትራ ያለውን ማኅተም ያረፈበትን የካርታውን ገጽ ሁለት ክፍል ማግኘት ስላልቻልኩና ይሄኛው የሚያሳየው ከጋንቤላ እስከ መተከል ወይም የዓባይ ግድብ እየተገነባ እስካለበት ስፍራ ያለውን ብቻ የሚያሳይ ስለሆነ በዚህ ስምምነት መሠረት እራሳቸው እንግሊዞች በሰዓቱ የሠሩትን ሌላ ሙሉ ካርታ አያይዤላቹህለሁ ይሄኛውን ካርታ ቀጭኗን መስመር ተከትላቹህ አሁን ካለው ካርታ ጋር አደራርባቹህ ተመልከቱት ሱዳን ለእኛ ልትሰጠን የሚገባት በርካታ መሬት እንዳለን ያመለክታል እንጅ እኛ ለሱዳን ልንሰጥ የሚገባን መሬት እንዳለ አያመለክትም!!!

ሱዳኖችም በዚህ ሰነድ መሠረት ወደፊት ድንበር መካለላችን ስለማይቀር ያኔ ከእነሱ ልንወስደው የምንችለው ተጨማሪ መሬት የሚኖረን መሆኑን ስለሚያውቁ ነው ይሄንን በእነሱ እጅ ያለንን በርካታ መሬት ለማስቀረት "ከእናንተ እጅ መሬት አለን!" እያሉ የሚያደነቁሩን!!!

እንደሚያስቡት ሞኝ ከሆንን ተጨማሪ መሬት ያገኛሉ። ከነቃንባቸውና "በስምምነቱ መሠረት ከእናንተ እጅ ለእኛ ሊሆን የሚገባ መሬት አለን!" ብለን ከያዝናቸው ደግሞ "በቃ እኛም አንጠይቃቹህም እናንተም አትጠይቁን!" ብለው መሬታችንን ለማስቀረት እንዲመቻቸው ነው አብዝተው እየጮሁ ያሉት!!!

እውነትም ስልታቸው ሳይሠራላቸው አልቀረም "አቦ ወደዚያ 'መሬታችን ነው!' የሚሉትን ሰጥተን እንገላገል!" የሚል ቂል ሰው እየበዛ መጥቷል። ሱዳኖች ሕሊና የሚባል ነገር የላቸውም። ውኃችንን በነጻ መጠጣታቸው ሳይበቃቸውና ትንሽም እንኳ ይሉኝታ ሳይሰማቸው ነው እንግዲህ በቆዳ ስፋታቸው ከአፍሪካ አንደኛና ግዚፍ ሆነው እያለ ከዚህም በላይ ለመግዘፍ መሬታችንንም ሊዘርፉን እየተስበደበዱ ያሉት!!!

ችግሩ በእኛ በኩል የሚታመን ሰው አለመኖሩ ነው። አገዛዙ የኢትዮጵያን ሕዝብ አጭበርብሮ "የእኛን አይደለም የወሰዱት የራሳቸውን ነው!" ብሎ ሰፊ መሬት ለሱዳን መስጠት የሚፈልግ መሆኑና በትክክል የሚሚገትልን አለመሆኑ ነው ችግሩ። አሁን ደግሞ ጭራሽ የኢትዮጵያን ሕዝብ አጭበርብረው የሚያግባቡለትን ምሁራን ተብየዎችን በየሚዲያው አሰራጭቶ እኛ

"መሬታችን ነው ድንበራችን ነው!" የምንለውን እዚህ ጓንግ ወንዝ ምላሽ ያለውን ድንበር አላግባብ የያዝነው እንደሆነ አድርገው እንዲሰብኩ እያደረገ ነው ያለው። አስቀድሞ በዚህ የድንበር ጉዳይ ላይ በተቆርቋሪነት ሲሟገቱ የነበሩትን አንዳንድ ሰዎችን ሳይቀር አግባብቶና ደልሎ የራሱ አድርጓቸዋል!!!

ሀገሬው ግን መሬቱንና ድንበሩን ጠንቅቆ ያውቀዋል። ሱዳኖች ሻለቃ ጎየን እሱም እራሱ እንደገለጸው ከስምምነቱ ውጭ እንደፈለገ አድርጎ በመከለል ለምልክት ያስቀመጠውን ድንጋይ በየጊዜው ኪሎሜትሮችን እያሻገሩ እያመጡ ሲያስቀምጡ መኖራቸውን ጭምር ጠንቅቀው ያውቃሉ!!!

ደግነቱ በስምምነቱ ለምልክት የተጠቀሱት ተራሮችና ወንዞች የሚንቀሳቀሱ አለመሆናቸው ነው። ስምምነቱ ከሱዳን መንግሥት ጋር ሳይሆን ከቅኝ ገዥ ጋራ በርካታ መሬታችንን በኃይል ወስዶ በጫናና በማስፈራራት የተደረገ ስምምነት እንደመሆኑ የመቀበል ግዴታ የሉብንም እንጅ "እንቀበለው!" ብንል ግን እዚያ ሰነድ ላይ በሎንግቲዩድና በላቲቲዩድ ዲግሪ ጭምር የተገለጹ የመገናኛ መስመሮችን እንዲሁም የወንዝና የተራራ ምልክቶችን ተከትሎ መካለልና ከእነሱ እጅ ያለንን መሬት ገቢ ማድረግ ይቻላል። በዚያ ስምምነት መሠረት ስንካለል የምናገኘው ተጨማሪ መሬት ይኖረናል እንጅ የምንሰጠው አንዲት ስንዝር እንኳ መሬት አትኖርም!!!

በትክክል ግን የሱዳንና የኢትዮጵያ ድንበር መካለል ያለበት እነ ዐፄ ቴዎድሮስ ቱርኮችን ወይም ቱርካዊው ከዲብ ኢስማኤል የዓባይን ምንጭ ጣናንና አካባቢውን የግብጽ ግዛት ለማድረግ እንዲይዝ አዝምቶት የነበረውን የግብጽ ወራሪዎችን የዘጠኝ ቀን ጉዞ ወደ ሱዳን ውስጥ ተጉዘው ደባርኪ ላይ "ይሄ የኢትዮጵያ መሬት ነው ልቀቁ!" እያሉ እየሔዱ ይወጉ የነበሩበትን ታሪክ፣ በኋላም ዐፄ ምሊልክም ለእንግሊዝ፣ ለጣሊያንና ለፈረንሳይ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ግዛቴ የሚጀምረው ከቶማት (አሁን ካለው ድንበር 150ኪ.ሜ. ወደ ሱዳን ውስጥ ተገብቶ የምትገኝ ከተማ) ነው!" ያሉትን መሠረት ባደረገ መልኩ እኛ እና ሱዳኖች ነን መደራደርና መካለል ያሉብን እንጅ እንግሊዝ ለራሷ ጥቅም ጫና አሳድራና አስፈራርታ ለራሷ አድልታ የኢትዮጵያን መሬት ወደ እነሱ ጨምራ ያሰመረችላቸውን መስመር ዳኛ ወይም መሸማገያ አድርገን አይደለም ልንደራደርና ልንሸማገል የሚገባን!!! ይሄ እጅግ ሲበዛ ሞኝነትና የራስን ታሪክ መካድ ነው!!!

ይሄ ይሄ ውድ ዋጋ የተከፈለበት የድንበር ታሪክ ባይኖር ኖሮ እሽ "በሱዳን እጅ መሬት አለን!" ብለን የይገባኛል ጥያቄ ባላነሣንና ይሄንን የእንግሊዝን የድንበር መስመር ሳናቅማማ በተቀበልን ነበር። ነገር ግን ከእንግሊዝ በፊት ያ ሁሉ ዋጋ ሲከፈልበት የኖረ ድንበር የማስከበር ታሪክ እያለን ግን እንግሊዝ በጫናና ማስፈራሪያ ስንት መሬት አልፋ መጥታ እንደፈለገች ያሰመረችውን መስመር ለመቀበል የምንገደደው በምን አግባብ ነው???

"መሬቱን ለዘላለም የራሴ አድርጌ ስጠቀምበት እኖራለሁ!" ብላ ጎምጅታ ጫና አሳድራና አስፈራርታ እንዲህ ያደረገችን እንግሊዝ በቦታው በሌለችበት ሁኔታ እኛ ስንት መሬታችንን ያስቀረብንን ይሄንን የተናጠል የድንበር መስመር ተቀብለን የምንቀርበት ምናችን ሞኝ ነው??? ንብረቱን ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድ ወይም በጉልበት የተቀማ ሰው በጉልበተኛ ያለ አግባብ የተወሰደበትን ንብረቱን ለማስመለስ ቀን ይጠብቃል እንጅ እንዴት አሜን ብሎ ሊቀመጥ ይችላል??? አሜን ብሎ ሊቀመጥ እንደማይችል እነሱ ፈጽሞ ይሉኝታን በማያውቅ ስግብግብ አቀራረብ የማይገባቸውን ከመጠየቃቸው ማረጋገጥ ይቻላል!!!

የእኛ ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ሱዳኖችስ እንዴት ብልጥ ቢሆኑ ነው ከእነሱ ጋር ያላደረግነውንና በጉልበተኛ "የግድ ተቀበሉ!" ተብለን የተጣሉብንን የድንበር ስምምነትን "ተቀበሉ አክብሩ!" የሚሉት??? ይሄ የድንበር ስምምነትኮ የአፍሪካ ኅብረት "ይጽና!" እንዳለው እንደሌሎች ቅኝ ተገዥ ሀገሮች የአንዱ ቅኝ ገዥ ከሌላው ቅኝ ገዥ ጋር ተስማምቶ ያደረገው የድንበር ስምምነት አይደለም እኮ። ስለሆነም ልንገዛበት አንገደድም ማለት ነው። እኛ ነጻ ሀገር እንጅ ቅኝ ተገዥ ሀገር አይደለንም!!! እንደ ነጻ ሀገርነታችን ድንበራችንን የምናውቀውና የምንከልለው እኛ እራሳችን ነን!!!

ያውም እኮ እዚህ ካርታ ላይ ማኅተማቸው እንዴት እንደሰፈረ እንጃ እንጅ ከታሪክ እንደምንረዳው በስምምነቱ ወቅት ዐፄ ምኒልክ የተሰመረው ካርታ ወደሱዳን ያስገባው ቁልፍ ቁልፍ ስፍራ ሲነገራቸው "አይ ይሄማ አይሆንም!" ብለው ስምምነቱን አለመቀበላቸውንና በሰነዱ ላይ በሰፈረው ቃል መሠረትም መሬት ላይ ምልክት ለማስቀመጥ ወይም ለመካለል በሚል ከሻለቃ ጎየን ጋር ሰው ሔዶ አለመካለሉን ነው የምናውቀው!!!

እንግዲህ ይሄ ይሄ ሁሉ ጠንካራ የመከራከሪያ ነጥብ ነበረን ምን ዋጋ አለው ለባዕድ እንጅ ለሀገሩ የሚል፣ የሚያስብ፣ የሚቆረቆር፣ የሚሟገት፣ የሚቆጭ መንግሥት የለንም ማን ብሔራዊ ጥቅማችንን፣ ድንበራችንንና ሉዓላዊነታችንን ያስከብርልን???

መግቢያየ ላይ እንዳልኩት አገዛዙ ከባድ ቁማር ሊቆምርብን የተዘጋጀ ይመስለኛል። ከላይ እንዳልኳቹህ እራሱ አስገብቷቸው አስይዟቸው ሲያበቃ የግድቡን ጉዳይና ሌላም ሌላም ነገር እያነሣ "ወቅቱና ሁኔታው ምቹ አይደለም!" ምንንትስ ምንንትስ እያለ እያመሀኘ ሳያስወጣ አስይዟቸው ሊቀር ነው ፍላጎቱ!!

በርካታ ገበሬ ከስፍራው ከተፈናቀለበት ከአማራ ሕዝብ ወይም የአማራ ክልል ከሚለው ጥያቄ ሲመጣበትም ከላይ የጠቀስኩትን ማመሃኛ እየጠቀሰ ይዘውት እንዲቀሩ ለማድረግና "እንችላለን ካላቹህ እራሳቹህ ተዋግታቹህ አስወጡ!" እያለ ሊሳለቅብን የተዘጋጀ ይመስለኛል።

አገዛዙ መሰለው እንጅ ግብጽ የጦርነቱን መልክ ከድንበር ይገባኛል ወደ ወረራ ጦርነት ለመቀየር ከኋላ እየሠራች በመሆኑ እንዲህ ብሎ ሊሳለቅብን የሚችልበትን ዕድል ሊያገኝ የሚችል አይመስለኝም!!!

እኛ ግን እንደምታዩት የዜግነት መብት ተነፍጎን በገዛ ሀገራችን ስደተኞችና መጻተኞች ሆነን እጅግ በሚያሳዝንና ለማመን በሚያቅት ሁኔታ በራሱ በአገዛዙ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ እየተፈጸመብን የቆየና አሁንም ያለ በመሆኑ አገዛዙ ይሄንን ግፍ ለማቆም ቃል እስካልገባና ለግፍና ሰቆቃ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋው ሰለባ ወገኖቻችን ካሳ እስካልከፈለ ጊዜ ድረስ ይህ የግብጽና የሱዳን የወረራ ጦርነት በመጣ ጊዜ ከአገዛዙ ጎን ተሰልፈን መዋጋት አይኖርብንም!!!

ለማን ብለን ነው የምንዋጋው??? ሀገራችንን እኮ ተቀምተናል። ለጠላታችን ጥለናት ተጨፍጭፈን ለምንጠፋባት ሀገር ነው እንዴ የምንዋጋው??? ትውልዳችን የሚቀጥል ቢሆን እናኳ እንኳ እንደወትሯችን "ሀገራችን!" ብለን በዜግነት ግዴታችን በተዋጋን ነበር። የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በሰፊው እየተፈጸመብንና ሩቅ ባልሆነ ጊዜ ከዚህች ሀገር ደብዛችን ለማጥፋት በከፍተኛ ደረጃ እየተሠራብን ግን በምን ሒሳብ ነው መሥዋዕትነት ለመክፈል የምንገደደው??? ለማን ብየ ነው ዋጋ የምከፍለው??? ጠላቴ ሀገር እንዲኖረው ብየ??? እንደ ወያኔ "ለግብጽና ለሱዳን ደግፈን በመቆም ባንዳ እንሁን!" አይደለም እያልኳቹህ ያለሁት። "እኛ ጠፍተን ሀገራችንን ለጠላታችን አውርሰን ለማኖር መዋጋት ወይም መሥዋዕትነት መክፈል የሌብንም እራሱ ይወጣው!" ነው እያልኳቹህ ያለሁት!!! "ሀገራቹህ ናት ዜጋ ናቹህ መዋጋት አለባቹህ!" ካለ ደግሞ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋውን ላይመለስበት አቁሞ ሀገራችንን ሀገራችን ያድርግ የዜግነት መብታችንንም ያክብር ይጠብቅ!!!

ወገኖቸ አቅም አልባ በተደረግንበት ሁኔታ ይሄንን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ማስቆም ካለብን እንዲህ ዓይነት ጠንከር ያለ የመደራደሪያ ነጥብና አቋም ይዘን በመቅረብ ነው ልናስቆመውና እንደዜጋ ተከብረንና መብታችን ተጠብቆ ልንኖር የምንችለው ሌላ ምንም የማስቆሚያ መንገድ ወይም bargaining chip የለንም!!!

አማራ እንደ አንድ political community እንዲህ ዓይነት ጨከን ያለ bargaining chip ይዞ ካልቀረበ በስተቀር አትጠራጠሩ በቅርብ ጊዜ ጠፊ ነው። bargaining chip ሲኖረን bargaining power ይኖረናል። bargaining power ካለን ተሸናፊ አንሆንም። ፖለቲካ ማለት ጨዋታ ነው ወገኖቸ። መኖር ከፈለግን ጨዋታውን ችለን መጫወት ግድ ይለናል። ጨዋታውን ችለን ከተጫወትን ወይ እናሸንፋለን ወይ ደግሞ አቻ እንወጣለን። ይሄም ማለት ምንም የምናጣው ነገር አይኖርም ማለት ነው። ጨዋታውን አልቻልንበትም ወይም bargaining chip የለንም ማለት ግን bargaining power አይኖረንም ተሸናፊ እንሆናለን ማለት ነው። የተሸነፈ ደግሞ

የራሱ የሆነ ነገር አይኖረውም። እሱም እራሱ ምርኮኛ ነው። ህልውናው ባሸነፉት አካላት እጅ ወይም ፈቃድ ስር ይወድቃል!!!

ያሸነፉት ወይም ጠላቶቹ ደግሞ እሱን የማጥፋት ሰይጣናዊ ዓላማ ያላቸው ከሆኑ በቀላሉ ሊያጠፉት ይችላሉ ማለት ነው። እናም እንደ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ፖለቲካን እንዲህ አስልተን መጫወት አለብን እንጅ ዝም ብለን እንደከዚህ ቀደሙ በዘልማድ በእውር ድንብስ መጓዝ አይኖርብንም። ይሄ ዘልማዳዊ የእውር ድምብስ አካሔድ ብዙ አስበልቶናልና ከዚህ መውጣት አለብን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው